ስለ ራስ

ESTIFANOS WEGAYEHU

2014 EC

[estifanoswegayehu17@gmail.com]

ምስጋና

መላዕክት በሰማይ ሙዚቃ ሲያደምጡ

ላንዱ እምላካቸው ክብሩን ሊገልፁለት ሬጌን መረጡ

ምስጋና ለፈጣሪ እልልታ ሆነ

አምላኩ ዘንድ ቀርቦ ቦብ ማርሌ ዘፈነ

ሀሴት ሞላ በልባቸው ፍጥረታት ተደሰቱ

ከደስታቸው ብዛት ቅዱሳን ተነስተው ለአምላክ ሰገዱ

ለአለም እንዲበቃ በሬጌ መዝሙሮች ፍቅሩን አዳረሱ

የሰማይ ወንዞች ወደ ምድር ፈሰው ከግዜን ደረሱ

እልልታ ለአምላክ እልልታ ለፈጣሪ

አትሳሳች ነብሴ ክብር ለሚገባው ለአንድዬ ዘምሪ

ውስጥ ነው ሚስጥሩ

የእንባዬ ጠብታ የልቤን ድርቀት ቁልቁል ሲያርሰው

አይኔ አፍስሶት የዘመናት ጥያቄዬን እንባዬ መለሰው

ብዙ ነው ተአምሩ

ውጪ ነው ያልኩት ውስጥ ነው ሚስጥሩ

እዛ ሆነህ ፍረድ

እባክህ ጌታ ሆይ የፍርድ ቀን ደርሶ ወደኛ አትምጣ

በምድር ስትኖር አይተኸዋልና የሰው ልጅን ጠረን የሰው ልጅን ሽታ

በተፈጥሮ ሚዛን

መንቃት የቻለው ብቸኛው ፍጥረት የሰው ልጅ አይደለም

የሰው ልጅ ቢጠፋ ለፍጥረታት ሁሉ ፍትሀዊ ናት አለም

ከመከበር በላይ መናቅ ያስተምራል

ህይወት የገባቻው ከትላንት ይማራል

እንደ ራስ

በመንጋ ከማሰብ ከራስ ጋር በመኖር ከራስ ጋር መታገል

በአካል ተመሳስሎ ከሰዎች መካከል በመንፈስ መነጠል

ሀቅ ነው ብለው ሰፍረው ካስቀመጡት ከትላንት እውነታ

በተረዳኸው ልክ ከዘልማድ እስር እራስህን ፍታ

አትፍረድ

በእለት ተእለት ኑሮ ከችሎቱ ቆመን

በፈረድነው ልክ ለፍርድ እንቀርባለን

በማለዳ መንቃት

ማለዳ ተነስቶ

ዝምታን መለማመድ

ከራስ ተጣልቶ

በሀሳብ መሰደድ

አንዳንዴ ቆሞ

አንዳንዴ መራመድ

ስሜትን አሸንፎ

እራስን መግዛት

እራስን መዝኖ

ዋጋ ማጣት

ለደስታም ለሀዘንም

እኩል መፈጠር

የሁሉም ነገር

በጊዜ መታጠር

በእምነት የሚገኝ

የመንፈስ ልዕልና

አላዋቂ ሆኖ

ማወቅ ነው ጥሞና

የሆነውን ማመን

ያመነውን መቀበል

መከተል

ፍቅርን ማፍቀር

አክብሮ መከበር

ተከብሮ ማስከበር

ባለማመን በንቃት

አይምሮን መሰለል

በማመን በእምነት

እራስን መጠለል

ሰዎች እስከ ዛሬ ኖርን የምንለው

እራሱን የደገመ አንድ ታሪክን ነው

የዩሀንስ ራዕይ

ከኖህ ዘመን አልማርም ብሎ የሰው ልጅ ዳገም መንገዱን ስቷል

በራዕይ እንደሚለው የመጨረሻው ቀን ከፊታችን ቀርቧል

ለፍላጎቱ ሲል ከእቃዎች በታች የሰው ልጅ እረክሷል

ሰው ነኝ ይላል እንጂ ሰው ከሰውነት አንሷል

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው

በመጨረሻው ቀን መጥፊያችን ማወቅ ነው

አዳምም ሲጣል አትወቅ ያለውን ማወቅን አውቆ ነው

በዚያን ጊዜ ተጠንቀቁ

በዚያን ጊዜ ደንቆሮዎች ብልሆች

ብልሆችም ደንቆሮዎች ይሆናሉ

ፍትህና ካልሲ

ፍትህን ፍለጋ ሄደን በየ ቢሮ

ያነባነው እንባ በየስንቱ ጓሮ

ቢረሳም ብዛቱ አስታዋሹ ጠፍቶ

ይናገራል ካልሲ ችሎት ላይ ጠንብቶ

እደርሳለው

ዛሬ ባልደርስም አንድ ቀን እደርሳለው

ቆም ብሎ ማሰብ ከመሄድ በላይ ነው

ፅናት

ከአለም ተለይ እንጂ

ፈጣሪን አትለየው

ይታያል ደስታቸው

መቆም የቻሉ

ብቻቸውን ሆነው

ፈቅረይ ናተይ

ብቸኝነት
ይሻለኛል ለኔ
ካንቺ ውጪ
ግጣሙን ፈልጎ
አያገኝም ጎኔ
ልርሳሽ ብል እንኳን
አረሳሽም እኔ

ስም እና እምነት

ስለ ፍቅር አምላክ

ስለ ፍቅር ጌታ

ማፍቀሬ ከገባት

ማፍቀሩን ተረድታ

ካመነችኝ ብዬ

የታቦታቱን ስም

ብዘረዝረው

እሷ ያመነችኝ

እጇን መትቼ

በስሟ ስምል

በዚም ዘመን

የተፈጥሮን ሰላም ማድመጥ ብንችል ኖሮ

ከባድ እንኳን ቢሆን አይከብደንም ኑሮ

90ዎቹ

ዘመኔን ነው ምመስለው ትውልዴን

በኔ ዘመን ላይ ሳልኳት ሀገሬን

ስም እንኳን ሲወጣ

ህሊና፣ ዝምታ፣ ትእግስት፣ ሰላም፣ ትህትና፣ ምህረት ተብሎ ነው

የኛ ዘመን እኛን ነው ሚመስለው

የገጣሚ ደብተር

በሀሳብ ምስቅልቅሎሽ ግጬት

እርቅ፣ ሰላም፣ ፍቅር የናፈቃት

ሁሉን አጥግባ እሷን ግን የራባት

ኮከብ ነኝ

ከውስጥ ባየሁት ልክ ከውጪ አይታይም

ከኔ በልጦ አለም አይገርምም

ሲታይ ቢያምር ቢያብረቀርቅም

የሰው ጌጥ የሰው ነው

እኔን አያደምቅም

ሰው የሚሆነው የሚያስበውን ነው

ካየነው ወይ ከሰማነው

ሁሉም ትንሽ ድርጊት የራሱ መልስ አለው

አይቶ እንዳላዩ ማለፍ

እርቃኗን አለም ስሎ ማሳለፍ

አዳሪ

በየ አስፓልቱ ዳር በየ ሸለቆው ስር
ሴትነት ሲረክስ ወንድነት ሲከብር
ደርሶ ከአፍንጫው ለጋለው ስሜቱ
ቀበቶ መፍታት ነው ለሱ ወንድነቱ
ቀሚስ መግለብ ነው ኒሻን ሽልማቱ
የሷ ምስኪን ገላ የእለት ጉርስ ፍለጋ
ሆድ አሸንፎት ወደቀ ለአልጋ
የራሱ አደረጋት ለሰአታት ገዝቶ
ሁሉን አጠናቆ ሲነሳ ተኝቶ
አዳሪ ይላታል አዳሩን እረስቶ

ያጤፋሪስ ሽታ

የማርክስ ጋርቬ

እሩቅ ያነገበ

የነፃነት ጥሪ

ትንቢቱ ሊፈፀም

ቃል ኪዳኑ ደርሶ

ከራስ ተፈሪ

ለጥቁር ህዝብ

አንድነት መቋጫ

ሰንደቅ ያነገበች

ሂዱ ወደ ምስራቅ

የቅዱሳን ሀገር

አንዷት ምድር አለች

ከኤደን ገነት

ከግዮን ምንጬ ስር

ሬጌ ሲሰማ

በፅናፅኑ ድምፅ

ፍቅር ትለብሳለች

ኪ ንግስተን በዜማ

ከናቲ ድሬድ

ከድሬድ ላክ ራስታ

ከጊታሩ ክር

ከከበሮ ድምድምታ

ከሩቅ ተመስጦ

ካጤፋሪስ ሸታ

ትዘላለች ነብሴ

ከሙዚቃው ገብታ

ኦሪጅናል የራስታ መንደሮችን ብቅ ብሎ ላየ

ከተፈጥሮ የተቀዳ

ተፈጥሯዊ

እውነተኛ ህይወት

እራስን ዝቅ አርጎ

ሀሴት ሚያጎናፅፍ

አይምሯዊ ብስለት

አሻግሮ የማየት

በጥበብ የመኖር

ጥበባዊ ኪነት

በ እኔና እኔ ስሜት

ሌላውን አካል

እንደ ራስ መውደድ

በውጣ ወረድ

ተደጋግፎ ማለፍ

በጋራ መራመድ

በፍቅር ታንኳ

ባንድነት ሰንሰለት

ከሁሉ መዛመድ

ከውጫዊው ይልቅ

ለውስጣዊው ውበት

ክብርን መስጠት

በማሪዋና ጥቅል

በተመስጦ

እራስን መመልከት

በሀሳብ ተጉዞ

እስካለም ዳርቻ

ተፈጥሮን መቃኘት

የባቢሎን እውቀት

ያላግባብ ምርምር

አይናችንን አልፎ

ማየት ያልጋረደን

የእግዚአብሔርን ተአምር

ስልጣኔ ያልበረዘው

በተስፋይቱ ምድር

የሚኖር ባህታዊ

ባዶ እግሩን ተጉዞ

ሻሸመኔ የደረሰ

ጢማም ናዝራዊ

ቀስተ ደመናን ጨብጦ

መልክትን ያዘለ

ለግርማዊ ቀዳማዊ

ከጥቁር አምላክ

ባምሳሉ ተፈጥረን

ከአፍሪካ ምድር

ጥቁር የወለደን

በጊታሩ ዜማ

ስቱዲዮ ገብቶ

ቦብ ማርሌ ያጠመቀን

ሬጌ ሙዚቃ

ከአለም ነጥሎ

ጠልቆ የማረከን

አንዳች ሳያጎድል

ለፈጠረን ፍጥረት

ለሰጠን ስጦታ

ክፉም ይሁን ደግ

ዘወትር ምስጋና

ለሀያሉ ጌታ

ባለዉ ተደስቶ
ለበጎ ነዉ የሚል
እንዲ ነዉ ራስታ

Respect